አፍንጫው በአፈር ትታሽ (ይዋረድ) አሁንም አፍንጫው በአፈር ትታሽ (ይዋረድ) አሁንም አፍንጫው በአፈር ትታሽ (ይዋረድ)" "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማንን ነው?" ተባሉ። እርሳቸውም "ከወላጆቹ ሁለቱን ወይም አንዱን በእርጅና ወቅት አግኝቷቸው ጀነት ያልገባ ነው።" አሉ።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው
ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "አፍንጫው በአፈር ትታሽ (ይዋረድ) አሁንም አፍንጫው በአፈር ትታሽ (ይዋረድ) አሁንም አፍንጫው
በአፈር ትታሽ (ይዋረድ)" "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማንን ነው?" ተባሉ። እርሳቸውም "ከወላጆቹ ሁለቱን ወይም አንዱን በእርጅና
ወቅት አግኝቷቸው ጀነት ያልገባ ነው።" አሉ።
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዱዓቸውን ጥግ ከማድረሳቸው የተነሳ አፍንጫውን አፈር ላይ እንደተደፋ ሰው በማድረግ በውርደት እንዲከናነብ ሶስት ጊዜ ረገሙት። የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማንን ነው የረገሙት? ተብለው ተጠየቁ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንዳቸውን ወይም ሁለቱን ወላጆቹ በእርጅና ወቅት አግኝቶ እነርሱ ጀነት ለመግባቱ ሰበብ ያልሆኑት ነው አሉ። ይህም የሚሆነው ለነርሱ በጎ ባለማድረጉና ሐቃቸውን በመንፈጉ ምክንያት ነው።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/3718